DISTRICT OF COLUMBIA
PUBLIC SCHOOLS

## SY23-24 የ‘PHELPS የምህንድስና (Architecture)፣ የግንባታ እና የኢንጂነሪንግ (Construction, and Engineering) ከፍተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት፣ የመግቢያ ሂደት የደረጃ መጠን (Admissions Process Rubric)

ከ9-12 ለሆኑ የክፍል ደረጃዎች

**ስለ ‘Phelps ACE’ ከፍተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የመግቢያ (Admissions) መስፈርት:** በ‘Phelps ACE’ ከፍተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ውስጥ፣ ችግሮችን የሚፈቱ፣ በስራ መስክ የቴክኒካል የትምህርት ፕሮግራማችን ላይ ፍላጎት ያላቸው፣ እና መፍትሄን ለማግኘት ሲባል ፈታኝ በሆኑ ነገሮች ውስጥ ለመስራት ፈቃደኛ የሆኑ ምሁራኖችን ማግኘት እንፈልጋለን። ምንም እንኳን የውጤት ደረጃቸው ወይም ያስመዘገቡት ውጤቶች ምርጥ ነው ባይባልም እንኳን፤ በክፍል ስራዎቻቸው ላይ ጥረት የሚያደርጉ፣ በይበልጥ ስኬታማ የሆኑ አመልካቾችን እንፈልጋለን።

**ስለ‘Phelps ACE’ ከፍተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የመግቢያ (Admissions) ሂደት:** በ‘Phelps ACE’ ከፍተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ውስጥ፣ የመግቢያ (admissions) ሂደታችን የሚያካትተው፣ ጽሁፍ (essay)፣ ቃለ-መጠይቅ፣ እና ሁለት የድጋፍ መስጫዎችን (recommendations)ን በMy School DC ማመልከቻ አማካኝነት ማስገባት ነው። ለእያንዳንዱ እጩ፣ እያንዳንዱን የመግቢያ (Admissions) ክፍሎችን ከግምት ውስጥ የምናስገባ እና ሁሉም አመልከቾች አንድ ዓይነት በሆነ የደረጃ መጠን (rubric) ይመዘናሉ። ምንም፣ አንድ-ብቻ የሆነ የመግቢያ (Admissions) ክፍል፤ ብቻውን ለብቁነት መወሰኛ ሆኖ አይወሰድም። ሁሉም ተማሪዎች፣ ለመግባት (admission) ብቁነታቸው እንዲታይላቸው ከግምት-ውስጥ እንዲገቡ ለማድረግ፣ የቃለ-መጠይቅን ማጠናቀቅ አለባቸው።

እያንዳንዱ ክፍሎች፣ ከዚህ በታች በሚገኘው ሰንጠረዥ መሰረት የደረጃ ውጤት (scored) የሚሰጠው እና የሚመዘን ይሆናል። በተለምዶ፣ በደረጃ መጠን (rubric) 15 ወይም ከዚያ በላይ ያመጡ ሁሉም ተማሪዎች ብቁ የሚሆኑ ሲሆን፣ ይህ በአነስተኛነት የሚጠበቀውን (minimum) የውጤት ደረጃ፣ በየዓመቱ ለእያንዳንዱ አመልካች፣ ሁሉን አካታች በሆነ ምልከታ አማካኝነት ወደ ዝቅተኛ ደረጃ የሚስተካከልበት ሁኔታ ሊኖር ይችላል። በአነስተኛነት ከሚጠበቀው (minimum) የውጤት ደረጃ በላይ ያመጡ ሁሉ አመልካቾች ብቁ ይሆናሉ፤ እንዲሁም አመልካቾች በተጠራቀመው የደረጃ መጠን (rubric) መሠረት አድርጎ በተከተለ አሰራር ደረጃ እንዲያገኙ ይደረጋል።

DISTRICT OF COLUMBIA
PUBLIC SCHOOLS

| የመግቢያ (Admissions) ክፍሎች | መለኪያ (Weight) | ማስታወሻዎች፡ |
|---|---|---|
| የቀለም ትምህርት የመስፈርት ምልከታ (GPAን እና በትምህርት ገበታ መገኘትና አለመገኘት/attendance የሚያካተተ) | 40%<br>(12/30 ነጥቦች) | የ'Phelps ACE' ከፍተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት፣ የውጤት (GPA)ን እና በትምህርት ገበታ መገኘትና አለመገኘት (attendance)ን፣ እንደ የቀለም ትምህርት የመስፈርት ምልከታ ይመለከተዋል። ምንም ዓይነት፣ በአነስተኛነት የሚጠበቅ (minimum) GPA እና በትምህርት ገበታ መገኘትና አለመገኘት (attendance) መለኪያ አያስፈልግም፤ ነገር ግን ሪፖርት ካርድ መግባት አለበት።<br><br>በተለምዶ፣ በፕሮግራማችን ስኬታማ የሆኑ ተማሪዎች የ2.5 GPA ወይም ከዚያ በላይ እና የ90% ወይም ከዚያ በላይ በክፍል ውስጥ መገኘት (in-seat attendance) ያላቸው ሲሆን፤ ሆኖም፣ አነስተኛ GPAዎች ያሏቸው ተማሪዎች፣ ትክክለኛ የሆነ እርዳታን እና ስልቶችን ሲያገኙ ስኬትን ማግኘት እንደሚችሉ ማወቅም ችለናል። |
| ቃለ-መጠይቅ | 40%<br>(12/30 ነጥቦች) | የ'Phelps ACE' ከፍተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት፣ በፕሮግራማችን ላይ ፍላጎት ያላቸውን፣ እና ችግሮችን ለመፍታት ፈቃደኝነትን የሚያሳዩ ተማሪዎች ለመለየት ጠንካራ እምነት አለው። የወደፊት ተማሪዎቻችንን ለመተዋወቅ የምንፈልግ እና ይህንንም ለማድረግ የቃለ-መጠይቁ ጠቃሚ መንገድ ነው።<br><br>ተማሪዎች ወደ ቃለ-መጠይቁ፤ ከቤተሰብ አባል ጋር (ከወላጅ፣ ሕጋዊ አሳዳጊ፣ ወይም ከሌላ የቅርብ የቤተሰብ አባል) ወይም ሌላ በህይወቱ ውስጥ ጉልህ አስተዋጽዖ ያለው ሰው ጋር (እንደ አሰልጣን፣ አማካሪ፣ ወይም የሕይወት መሪ/mentor)፤ ተማሪዎችን በመደበኛነት ከሚረዷቸው ጋር አብረው እንዲካፈሉ እንጠይቃቸዋለን።<br><br>በጤና መመሪያ እና በቤተሰብ ሁኔታዎች ላይ መሠረት ባደረገ-መልኩ፤ ለSY23-24 ቃለ-መጠይቆች፣ እንደየአስፈላጊነቱ እና በሁኔታዎች-አመላካችነት ላይ መሠረት በማድረግ፣ በርቀት (virtually) የሚሆንበት ሁኔታ ሊኖር ይችል-ይሆናል። |

DISTRICT OF COLUMBIA PUBLIC SCHOOLS

| | | |
|---|---|---|
| ጽሁፍ (Essay): በMSDC ማመልከቻ ውስጥ | 10% (3/ 30 ነጥቦች) | ልክ እንደ ቃለ-መጠይቁ፣ በፕሮግራማችን እና በጽሁፍ ንግግር (communication) ችሎታዎች ላይ፣ የተማሪው ፍላጎት ምን እንደሆነ ለማወቅ፣ ጽሁፉ (essay)ው ጥቅም-ላይ ይውላል። ይህ ጽሁፍ (essay)፣ እንደ MSDC ማመልከቻ አንዱ አካል በመሆኑ ይጠናቀቃል።<br><br>ጽሁፎች፣ ለሁሉም አመልካቾች ጥቅም ላይ በሚውለው ውስጣዊ የደረጃ መጠን (rubric)፣ ለተማሪውን የብቁነት የውጤት ደረጃ (score) ሲቆጠር፣ 10% በሆነው የጽሁፍ ውጤት ደረጃዎቹ ላይ የሚገመገም ይሆናል። ምንም እንኳን ተማሪዎች በከፍተኛ ደረጃ ትምህርታቸው ወቅት በሙሉ አዘውትረው መፃፍ ቢጠበቅባቸውም፣ ለጽሁፍ (essay) የደረጃ መጠኑ (rubric)፣ በቴክኒካል የአፃፃፍ ችሎታዎች ላይ፤ እንደ ሰዋሰውና ቃላት (grammar and vocabulary) ላይ ያተኮረ አይሆንም። |
| ድጋፍ መስጫዎች (Recommendations) | 10% (3/ 30 ነጥቦች) | የ'Phelps ACE' ከፍተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት፣ የተማሪውን የትምህርት ቤት ውስጥ ተሞክሮ የበለጠ ለመረዳት እና ለሪፖርት ካርዳቸው ይዘትን ለመስጠት በማለት፤ የአስተማሪን ድጋፍ መስጫዎችን (recommendations) ይጠቀማል።<br><br>ሁለት ድጋፍ መስጫዎች (recommendations) እንዲቀርቡ እንጠይቃለን። በተጠየቀው አስተማሪ አንድ ብቻ ተሞልቶ ከተጠናቀቀ፣ በገባው አንድ ድጋፍ መስጫ (recommendation) ላይ መሠረት በማድረግ ተማሪውን እንገመግማለን። ምንም ዓይነት ድጋፍ መስጫ (recommendations)ን ካላስገቡ፣ ትምህርት ቤቱ የ10% መጠን (weight) ወደ ቃለ-መጠይቁ ይጨምራል። |